# እኔ ለምን ልሙት ?!

(አሥራደው ከፈረንሳይ)

እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?
ልቤ ለምን ይተው ደም ማሰራጨቱን ?
ለምንስ ያቆማል አይምሮዬ ማሰብ ?
እንዴትስ ይከልከል ሳንባዬ አየር መሳብ ?
ለምን እሞታለሁ ለማን ይድላው ብዬ ?
ለምንስ ልሰደብ የሞተ ! ተብዬ ?
ለምን ተገንዤ በሳጥን ልጨመር ?
ቄሶችንስ ለምን በፍታት ላስቸግር ?
እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?!
ዕድሜ አራዝማለሁ ለቅማል ለትኋን ::

እንደምን ልከልከል ብርሃንና ፀሐይ ?
ለምንስ ይጫነኝ አፈርና ድንጋይ ?
ከርሃብ ከጥማት ከመቸገር በላይ፤
እየተቀበልኩኝ መከራና ስቃይ ::
ምን በደልኩኝና ሞት እኔጋ ይመጣል ?!
ለምን እሞታለሁ ? ሰው እንዴት ያሾፋል !
እኔ ለምን ልሙት ለምን አፈር ልሁን ?!
እድሜ አራዝማለሁ ለቅማል ለትኋን ::

ለምን ብሎ ይተው እግሬ መራመዱን ?
እጆቼ መጨበጥ ክንዴ መመከቱን፤
ጆሮዬ ማዳመጥ ዓይኔ መመልከቱን፤
አፍንጫዬ ማሽተት አፌ መናገሩን፤
ሆዴ መታዘቡን አንጀቴ ማዘኑን፤
ጥርሴ ፈገግ ማለት ልቤ መሸፈቱን ::
እኮ !

ምን በደልኩኝና ሞት ወደኔ ይመጣል ?
እኔ አልሞትም ከቶ ! ሰው ለምን ያሾፋል ?!
እኔ ከሞትኩማ ከተጫነኝ አፈር፤
እንዴት ይኖራሉ ቅማልና ትኋን፤: ቁንጫና መዥገር ?!

ሚያዝያ 20/2003 ዓ.ም.(28/04/201)

EthioLion.com